

# ስደተኞች ድምጽ መስጠት ስለሚችሉበት ሁናቴ እና በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ሁሉን ኣካታች የሆነ እንቅስቃሴን  በተመለከተ

促進會 華人權益 CAA
CHINESE FOR AFFIRMATIVE ACTION

Immigrant Parent Voting Collaborative

**AUTHORS**
Ron Hayduk *Professor, San Francisco State University*
Megan Dias *Ph.D. Candidate, University of Texas at Austin*
Olivia Marti *Ph.D. Student, University of California, Los Angeles*

# ኣጠቃላይ ሃሳብ

ይህ ሪፖርት በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ስደተኞች ድምጽ መስጠት የሚችሉበትን ሕግ ለማርቀቅ የሚካሄደውን ትግል ለማሸነፍ የሚደረገውን ጥረት የሚያመላክት አጠቃላይ እይታን ያቀርባል፣ ህጉ “ዜጋ ያልሆኑ ሰውች ድምጽ ስለመስጠት” ሊባል የሚቻል ሲሆን፡ ዜግነት የሌላቸ ሰውች ድምጽ መስጠት መቻላቸው፡ በአጠቃላይ የከተማው ምህዳር ውስጥ የስደተኞች በሁም መስክ የበቁ ይሆኑ ዘንድ ያለውን በጎ ተጽእኖ ያሳያል።[1] ለ10 ወራት ያህል ጊዜ ፣ ኣንድ የተመራማሪዎች ቡድን በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ ውስጥ ስላለው ስደተኞ የመምረጥ መብት የተመለከተውን ፕሮግራም፣ስደተኞች የምርጫ መብቶቻቸውን ለመጠቀም የሚያጋጥሟቸውን መሰናክሎች፣ እነዚህን ተከታታይ እንቅፋቶች ለማለፍ የማህበረሰብ ድርጅቶች የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች እና ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ምክሮችን ጨምሮ ስለ ከተማዋ የስደተኞች ድምጽ አሰጣጥ ፕሮግራም ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ከሰጡ 72 የማህበረሰብ አባላት እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ቃለ ምልልስ እና የትኩረት ቡድኖች ዉይይት አድርጓል። የምርምር ቡድኑ ከህዝብ ቆጠራ እና የምርጫ መረጃዎች፣ የመንግስት እና የፖሊሲ ዘገባዎች፣ የዜና ዘገባዎች እና ምሁራዊ ስራዎችን ጨምሮ ከህዝብ መዝገብ የተገኙ መረጃዎችን እንደ ግብኣት ተጠቅሙዋል። ለምርምሩ የተጠቀምንባቸው ዘዴዎቻችንን እና ምንጮቻችንን ከዚህ በታች የገለጽን ሲሆን፥ ቃለ፡መጠይቁ ላይ የተሳተፉትን ስም ዝርዝር በዚህ ዘገባ መጨረሻ ላይ እናቀርባለን። የጥናታችንን ቁልፍ ግኝቶች ኣጠቃላይ ነጥቦች በመግለጽ እንጀምራለን።

## የስደተኞች ድምጽ የመስጠት መብቶች ድጋፍ


በሁሉም ቡድኖች ውስጥ ያሉ ያነጋገርናቸው ሰዎች ፣ ወላጆች ፣ የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ሰራተኞች፣ የመንግስት ባለስልጣናት እና ምሁራን ፡ ስለ ስደተኛ ድምጽ የመምረጥ መብት መገንዘብ በመቻላቸው እንደተደሰቱ ገልጸውልናል። በቃለ-መጠይቁ የተካተቱት ሰዎች እንደገለጹት፥ ዜጋ ያልሆኑ ሰዎች ድምጽ መስጠት መቻላቸው፡የስደተኞች ድምጽ እንዲሰማ ለማረጋገጥ፣ በትምህርት ቤት ቦርድ ውሳኔዎች ላይ የልጆቻቸውን የትምህርት ገበታዎች ለማሻሻል፣ ስደተኞች ለተለያዩ ደረጃውች እንዲብቁ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ለማጎልበት፣ እንዲሁም ዘር ተኮር ያልሆነ ፍትሕ እንዲረጋገጥ ለማስቻል እና ሁልንም በእኩልነት እንዲካተቱ የሚያድርግ ነው በማለት ኣስረግጠዋል።

## ትረምፕ እና የፌደራል ኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ ህግ የደቀኑት ስጋት

የሳን ፍራንሲስኮ የድምጽ አሰጣጥ ህግ መጽደቅ፡ በ2016 ዓ.ም. የዶናልድ ትራምፕ ምርጫ ጋር የተገጣጠመ ሲሆን፣ ይህም ምርጭ አዲሱን ህግ ተግባራዊ ለማድረግ ልዩ ፈተናዎችን ደቅኑዋል። የመራጮች ምዝገባ መረጃ ሚስጥራዊ ስላልሆነ፣መጤዎች ለመምረጥ ከተመዘገቡ እስራት ወይም ዜግነት ለማግኘት ያለውን ሂደት እንዳያወሳስባቸው ስለሚሰጉ ፣ይህም በአንጻራዊነት ዝቅተኛ የስደተኛ የመራጮች ምዝገባ እና ተሳትፎ እንዲኖር አስተዋጽኦ አድርጓል።

## የቋንቋ እንቅፋቶች

የሳን ፍራንሲስኮ በሚችሉት ቋንቋ የመገልገል ድንጋጌ ቢኖርም፣ ስደተኞች የመምረጥ መብታቸውን በሚገባ ለመጠቀም የቋንቋ መሰናክሎች እና ተግዳሮቶችን ፈጥረዋል።




[1] በዚህ ዘገባ ውስጥ፣ የተለያዩ ቃላትን በተለዋዋጭነት ተጠቅመናል፡ “ስደተኛ ድምጽ መስጠት”፣ “ዜጋ ያልሆነ ድምጽ መስጠት”፣ “የነዋሪ ድምጽ መስጠት”፣ “የአካባቢ ዜግነት” እና “የመጤ ሰዎች ምራጭነት” ፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ በመሠረቱ አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው፡ የመምረጥ መብትን ማስከበር ወይም ወደነበረበት መመለስ። የዩኤስ ዜጎች ስላልሆኑ በአሁኑ ጊዜ ከመራጩ የተገለሉ የክልል ነዋሪዎች። በውጭ አገር የተወለዱ ዜግነት የሌላቸው ስደተኞች እና በውጭ ሀገር ተወላጅ ሆነው የዩኤስ ዜግነትን ያገኙ መጤዎች በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ እና ተጨባጭ መረጃዎች በሚፈቅድበት ሁኔታ ለያይተን ለማየት ሞክረናል።

## የእውቀት ማነስ እና የጊዜ እጥረቶች

ብዙ ስደተኛ ወላጆች ከልጆቻቸው ትምህርት ቤት ማስታወቂያ ገጽ ላይ እና በምርጫ ዲፓርትመንት ድህረ ገጽ ላይ ኣዲሱን የምርጫ መብትን የተመለከተ መረጃ ቢኖርም፣ ይህ መብት እንዳላቸው እንደማያውቁ ተናግረዋል።

## ቀደም ያሉ ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ኣሉታዊ ተሞክሮዎች

ድምጽ የመስጠት መብት ከማይፈቅዱ እና ድምጽ መስጠት ከሚያስቀጣባቸው ሃገሮች የመጡ ስደተኞች፡ እዚህ በምርጫ የመሳተፍ እድላቸው አነስተኛ ነው።

## “የመደራጀት ኃይል እንጂ ፍርሃት አያስፈልግም”

የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ቡድን፡ ድምጽ የሚሰጡ ስደተኛ ወላጆችን ህብረት (IPVC) አቋቁሞ ሰፊ ምርጫን የተመለከተ የትምህርት እና የተለያዩ አገልግሎቶችን ከመስጠቱ በተጨማሪ፡ በአስር ሺዎች ለሚቆጠሩ የስደተኛ ተንከባካቢዎች እና ሞግዚቶች በትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች እንዲሳተፉ አድርጓል። የመብት ተሟጋቾች ይህንን ሰፊ በትምህርት ቤቶች ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ፡ ለቁጥር እና ለስሙ ከሚደረጉ የመራጮች ምዝገባ ባለፈ እንደ “ስኬት” ይመለከቱታል። እነዚህ የመብት ተሟጋቾች በተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖች መካከል ትብብር እና ወዳጅነት እንዲገነቡ በማድረግ (የላቲን ኣመሪካ፣ የኤሲያ ኣመሪካውያን እና የፓስፊክ ደሴቶች ተወላጆች፣ የኣፍሪካ፣ የኣረብ፣ እና የኣፍሪካ ኣሜሪካውያን) ይህም ቀጣይነት ያለው የህዝባዊ መሠረት ግንባታ ጥረቶቻቸውን በማጎልበት፡ስደተኞችን ለከፍተኛ ደረጃዎች ለማብቃት እና ለማበረታ ት የሚደረጉ የጋራ ጉዳዮችን ይደግፋሉ።

## የሕግ ተግዳሮቶች እና ሌሎች ተቃውሞዎች

በሳን ፍራንሲስኮ የመጤዎች የመምረጥ መብት የሚፈቅደውን ህግ የሚቃረን የፍርድ ቤት ጉዳይ፡ በሳን ፍራንሲስኮ እና በሌሎች ተመሳሳይ ህጎችን ማስፈጸም በሚፈልጉ ከተማዎች ውስጥ፡ ይህን የስደተኞችን የመምረጥ መብት በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ፈተናዎች ጋርጦዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኣንዳንድ የመብት ተሟጋቾች፡ ይህን የስደተኞችን የመምረጥ መብት ኣጥብቆ መገፋፋት፡ ሌሎች ለስደተኞች ተስማሚ የሆኑ ህጎችን አደጋ ላይ ይጥላል የሚል ስጋት ኣላቸው። በተጨማሪም ስደተኞችን ለመጠበቅ እና የስደተኞች መብትን ለማስከበር ቀጣይነት ያለው ጥረቶች፡ በፀረ፡ስደተኛ ቡድኖች ኣሉታዊ ምላሽ ሊፈጥር ይችላል ብለውም  ይጨነቃሉ ።

## የስደተኞች ድምጽ የመስጠት መብት የወደፊት ዕጣ

በካሊፎርኒያ ውስጥ የሚኖሩ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የስደተኛ ቤተሰቦች እና እጅግ ብዙ የስደተኛ ተሟጋች ድርጅቶች በመኖራቸው እና የእነዚህም ሰፊ ኔትወርክን ከግምት ውስጥ በማስገባት፡ ወደፊት ብክፍለሃገሩ ለየት ያለ መልካም እድሎችን ያመጠል የሚል ተስፋ ኣለ። እነዚህን ተግዳሮቶች ለመመከት እና እድሎችን ለመጠቀም፡ የቻይናዊያን፡ ለአወንታዊ እርምጃ (CAA) እና ድምጽ የሚሰጡ ስደተኛ ወላጆችን ህብረት (IPVC)፡  በመጋቢት 2023 ዓ. ም.  ከካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ የተውጣጡ 75 የስደተኞች ድምጽ ባለድርሻ አካላትን በመሰብሰብ ወደ ፊት የስደተኛ ድምጽ መስጠት መብትን በሚገባ የማስፈጸም እንቅስቃሴን የሚጎለብትበትን ሁኔታ ተወያያቶ ነበር። ከስብሰባው በኋላ፣ በግዛቱ የሚገኙ እነዚህ የመብት ተሟጋቾች፡ ስለወደፊቱ የህግ እና የአተገባበር ተግዳሮቶችን በኣሸናፊነት ለመወጣት የሚረዱ መንገዶችንና ዘመቻዎች ለመቀየስ በየጊዜው ይገናኛሉ።

## ለሳን ፍራንሲስኮ እና ሌሎች የኣስተዳደች ግዛቶች የሚረዱ ምክረ ሃስቦች

ቃለ መጠይቅ ያደረግናቸው የመብት ተሟጋቾች፣ ተንከባካቢዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች እና በህዝብ የተመረጡ ባለስልጣናት፤ የሳን ፍራንሲስኮን የስደተኞች ድምጽ አሰጣጥ ፕሮግራምን ለማሻሻል ይረዳሉ የሚሉዋቸውን የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦችን ሰጥተዋል። እነዚህ ምክረ ሃሳቦች የስደተኛ ድምጽ አሰጣጥ ህግን ለመተግብር የሚሹ ለሎች ከተማውችም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

---

**ስደተኞችንና እነዚህን ስደተኞች የሚያገለግሉ ድርጅቶችን ማማከል፡-** የስደተኞችን የመምረጥ መብቶችን ለማስከበር፡ ስደተኞችንና እነዚህን ስደተኞች የሚያገለግሉ ድርጅቶችን ያማከለ መሆኑን ማረጋገጥ፤

---

**ባለድርሻ ኣካላትን ማስተፍ፡-** በሁሉም ሴክተሮች እና በማህበረሰቦች ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን ማቀናጀት ፤

---

**ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ፈንድ ማድረግ፡-** የባህላዊ ብዙህነትን እና ዴሞክራሲን ለማጠናከር ከመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን የመራጮችን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚረዱ ትምህርትን እና ተጓዳኝ አገልግሎቶችን የሚያካይዱ ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ፈንድ ያድርጉ ፤

---

**ውጤታማ የሆነ የግንኙነት እና የሚዲያ ስልቶችን በበርካታ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡-** በተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ የሲቪክ ቡድኖች እና የሚዲያ አውታሮች የሚተገበሩ ውጤታማ የግንኙነት እና የሚዲያ ስልቶችን በበርካታ ቋንቋዎች በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ አባላት ተደራሽ ማድረግ ፤

---

**ለስደተኞች በቂ ጥበቃ ማድረግ፡-** ስደተኞች በደህንነታቸው ላይ የበለጠ በመተማመን እንዲመዘገቡ እና ድምጽ እንዲሰጡ፣በተለይም ህጋዊ ዶኪመንት ለሌላቸው ፡ እንዲሁም ህጋዊ ወረቀት ያላቸው እና ህጋዊ ወረቀት የሌላችው  ሰዎች የተቀላቀሉባችው ቤተሰቦች የተሻሉ ጥበቃዎችን ያዘጋጁ፤